# ጠላት ወዳጅ ላይሆን…

(ከጋሻ ለኢትዮጵያ)

ምርጫ ዘጠና ሰባትን ተከትሎ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ግፍ ተፈጽሟል። በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ለእሥራት ሲዳረጉ በመቶ የሚቆጠሩ ሰላማዊ ዜጎች በሕወሃት/ኢሕአዴግ ደህንነት አባላት ተገድለዋል። ከጊዜ ወደ ጊዜ አገዛዙ የግፍ ጫና እያበዛ በመምጣቱ ሕዝቡ ሕወሃት/ኢሕአዴግ ካልተገደደ በቀር በፈቃዱ ስልጣን ሕዝብ ለመረጠዉ አካል እንደማያስረክብ ወደ ማመን እየደረሰ ነዉ።

በተለይ ደግሞ የቀድሞ ቅንጅት መሪዎች፣ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎችና ጋዜጠኞች ከሃያ ወራት በላይ ባላጠፉት ጥፋት በግፍ መንገላታታቸዉና የነመለስ ዜናዊ ሕወሃት/ኢሕአዴግ ቡድን በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የከፈተው ሽብር የጨለምተኝነት ደመና በአገራችን ላይ እንዲሰፍ አድርጎታል።

የኢትዮጵያ ህዝብ የሕወሐት/ኢህአዴግ የጥቃት ሰለባ በሆነበት ወቅትም በውጭ አገር የሚኖሩና የሕዝቡ አካል የሆኑ ኢትዮጵያዉያን በወገናቸዉ ላይ እያደረሰ የነበረውን መከራና ስቃይ ለተቀረው የዓለምአቀፉ ህብረተሰብ በማጋለጥ የታፈነዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ «ድምጽ» ሆነዉ ሲታገሉ ቆይተዋል።

በመሆኑም ከምርጫ ዘጠና ሰባት በፊት እንደ አንድ ለዲሞክራሲ የቆመ የአፍሪቃ መሪ አድርጎ እራሱን ለውጭው ዓለም ሲያስተዋውቅ የኖረው መለስ ዜናዊ ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ እርቃኑ ተገፎ ከነሮበርት ሙጋቤ እና ቻርለስ ቴይለር የባሰ ወንጀለኛ መሆኑ እየታየ ነዉ።

እንደ ክብርት አና ጎሜዝ (ከአውሮፓ ህብረት)፣ እንደ ኮንግረስማን ክሪስ ሰሚዝ፣ ሴናተር ራስ ፋይንጎልድ እና ኮንግረስማን ዶናልድ ፔን ያሉ አያሌ የአውሮፓና የአሜሪካ የተከበሩ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት አደገኛ ቦዘኔ (rogue) ቡድን ሲሉ የመለስ/ስብሃትን ሕወሃት/ኢሕአዴግ ቡድን ከፉኛ ሲያወግዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ በእንደዚህ አይነቱ የአደገኛ ቦዘኔ መንግስት ስር መውደቅ እንደማይገባው በአደባባይ መስክረዋል።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን በዲፕሎማሲው መስክ ባደረጉት ከፍተኛ ርብርብ በፈጠራ ወንጀል ተከሰው የእድሜ ልክ እስራት ተፈርዶባቸው የነበሩት መሪዎች እንዲፈቱ ለማድረግም ተችሏል።

የተፈቱት መሪዎች ለአፍታ እንኳ ሳያርፉ ሕዝብን የስልጣን ባለቤት ለማድረግ ተቋርጦ የነበረውን ትግል በአዲስ መልክ አደራጅተዉ እንቅስቃሴያቸዉን ቀጠሉ።

የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር እና በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነት ያተረፉት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ከገዢው ቡድን በኩል ይደርስ የነበረው ዛቻና ወከባ ሳይበገራቸዉ፣ ከሎሎች መሰል የትግል አጋሮቻቸዉ በመስራት የሕዝቡን ሞራል ገንብተው ወደ ዋናው የፖለቲካ መድረክ እየገሰገሱ ባሉበት ወቅት ነበር የአደገኛ ቦዜኔው መንግስት «ይቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም» በሚል መሰረተ ቢስ ዉንጀላ በማቅረብ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ከአሥር በማያንሱ የሲቪል ልብስ በለበሱ ጋጠወጦች እየተገፉና እየተዋከቡ ወደ ቃሊቲ እሥር ቤት እንዲወሰዱ ያደረገዉ።

ይህን አሳዛኝ ሁኔታ የተመለከቱት የ78 አመቱ አዛውንት ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም መለስ ብለው «ይሄ ሁሉ ግርግር ለምን አስፈለገ? አንዲት መጥሪያ ወረቀት ብታመጡ እኮ ይበቃት ነበር። የፈለጋችሁበት ቦታ

ድረስ ለመምጣት ትችል ነበር» ብለው አባታዊ ምክር ለመለገስ ሲሞክሩም አንድ የመለስ ታጣቂ ወመኔ እስኪንገዳገዱ ድርስ በሰደፍ ፊኛቸዉ ላይ መታቸዉ።

እውነት እኝህ አዛውንት ምን ወንጀል ሰለሰሩ ነው እንዲህ በአደባባይ የተመቱት? ወ/ት ብርትካንስ የትኛዉ ጥፋታቸዉ ነዉ ከአራት መኪናዎች በወረዱ አሥር ውርጋጦች እንደተራ ሌባ እየተገፈተሩ ወደ ቃሊቲ የሚወረወሩት?

እነዚህ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር እጅግ የታወቁ ሰላማዊና ጨዋ የአንድነት ፓርቲ አመራር አባላት እንዲህ እንደ ዕቃ እስር ቤት ከተወረወሩ፣ ሌላው ተራው የተቃዋሚ አባል ወይም ደጋፊ ዕጣ ፈንታ ምን እንደሚሆን ለመገመት አያዳግትም።

ጋሻ ለኢትዮጵያ የሲቪክ ማህበር :

- በስልጣን ላይ ያለው የህወሓት/ ኢህአዴግ መሪዎች የዛሬ 34 አመት በትግራይ በረሃ ህወሓት ሲመሰረት ጀምሮ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለማስገንጠል ስውር አጀንዳ ይዘው የገቡ ሰርጎ ገቦች የሚቆጣጠሩት የወንጀለኞች ቡድን ነው ብሎ ያምናል። ይህ የወንጀለኞች ቡድን ሕወሓት ለምን የሻዕቢያ ቅጥረኛ ተዋጊ ድርጅት ሆነ ያሉትን፣ ስለ ኢትዮጵያ አገራችን መፃኢ ህይወት የሚቆሮቆሩትን፣ የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ቀይ ባሕር ነዉ በሚል መርህ ይህ ታሪካዊ የባህር ድንበር ለኤርትራ አሳልፎ እንዳይሰጥ የተከራከሩትንና አሰተያየት ወይም ጥያቄ ያቀረቡትን ሁሉ ያለአንዳች ርህራሄ አስሮ የገረፈ እንዲሁም የገደለ ወንጀለኛ ድርጅት መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ነው ብሎ ያምናል።

- ይኸው የአደገኛ ቦዘኔዎች መንግስት ባለፉት 18 አመታት ብቻ በአገርና በወገን ላይ የፈፀማቸው እጅግ በርካታና ዘግናኝ ወንጀሎች እንደበቂ ማስረጃ ተወስደዉ የዚህ አጥፊ ቡድን አመራር አባላት የበለጠ ጥፋት ከማድረሳቸዉ በፊት ለፍርድ የሚቀርቡበትን መንገድ ማዘጋጀት አገሩን የሚወድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ኃላፊነትና ግዴታ ነው ብሎ ጋሻ ለኢትዮጵያ ያምናል።

- የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት ብርትካን ሚደቅሳ እና በሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞችን ለማስፈታት፣ እንዲሁም ወንጀለኛው ቡድን ከስልጣን ተወግዶ የነፃነት ችቦ እንዲቀጣጠል ጋሻ ለኢትዮጵያ ከወገኑ የሚጠበቅበትን ሁሉ ለማድረግ ያለዉን ጽኑ የትግል ቁርጠኝነት ያረጋግጣል።

የተባበረ ህዝብ ለድል ይበቃል!
ጋሻ ለኢትዮጵያ ጥር 2009
www.ethiopiangasha.org
admin@ethiopiangasha.org